








# ተግባራዊ ጸሎት

ትምህርት 7 ለ ግንቦት 8፣ 2018

"የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ፥ ልባችሁንም በፊቱ አፍስሱ፤ እግዚአብሔር ረዳታችን ነው።"

(መዝሙር 62:8)





ዓለም በዙሪያችን ብትነዋወጥም፣ ደግሞም ጸሎታችን ሳይመለስ ረጅም ጊዜን ቢወስድም “ዘወትር ጸልዩ” በማለት ጳውሎስ ይመክረናል (ኤፌ 6:18)።

በእነዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ የኤልያስን እና የሃናን ጸሎት ብንመለከት እንጠቀማለን ደግሞም እንበረታታለን።

ታዲያ እንዴት እንጸልይ? ስለምንስ እንለምን? በግላችን ወይስ በጋራ እንጸልይ? ጸሎት ለእግዚአብሔር እንድንነግረው ብቻ ሳይሆን እርሱን እንድናደምጠውም ጭምር ያስችለናል ወይ?









- በመከራ ጊዜ መጸለይ:
  - ኤልያስ: በቀውስ መሃል የሚደረግ ጸሎት
  - ሃና: የማይመጣ ምላሽ
- አርአያ የሚሆኑ ጸሎቶች:
  - ኢየሱስ: የጸሎት ይዘት
  - ዳንኤል: የጸሎት አወቃቀር
- ስለ ጸሎት አራት ጥያቄዎች




# በመከራ ጊዜ መጸለይ

# ኤልያስ፡ በቀውስ መሃል የሚደረግ ጸሎት

“እርሱም፡- ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ፤ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ አለ።” (1 ነገሥት 19:10)



እግዚአብሔር በቀውስ ውስጥ ስንሆን ጸሎታችንን የሚመልስልን እንዴት ነው?



ኤልያስ አጭር ጸሎት ከጸለየ በኋላ እግዚአብሔር ወዲያውኑ በእሳት መለሰለት (1 ነገ 18:36-38)።

ደግሞም ዝናብ እንዲመጣ ሰባት ጊዜ ከጸለየ በኋላ እግዚአብሔር ትንሽ የሆነች ደመናን ልኮ ከዚያ ወደ ኃይለኛ ዝናብና ነፋስ ቀየራት (1 ነገ 18:42-45)።



ኤልያስ ሞትን በለመነ ጊዜ እግዚአብሔር ዝም አለውና እንዲመግበው መልአክን ላከለት (1 ነገ 19:4-8)።



ኤልያስ ተስፋ ቆርጦ በዋሻ ውስጥ ሲጠባበቅ ሳለ በመጨረሻ የልመናውን ምላሽ እግዚአብሔር ሲመልስለት አደመጠ (1 ነገ 19:9-18)።



የአንዱ ምላሽ ፈጣንና ተዓምራዊ ነበር። የሌላኛው ግን ሰባት ጊዜ ከጸለየ በኋላ ነበር ዝናቡ የተላከው። ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ በሚያስፈልገው ሰዓት የሚያበረታታ ቃል የመጣለት ከ40 ቀናት ቆይታ በኋላ ነበር። እግዚአብሔር በተለያዩ ሁኔታዎቻችን ውስጥ እንዴት እና መቼ መመለስ እንዳለበት እርሱ ያውቃል።

# ሃና: የማይመጣ ምላሽ

"ስለዚህ ሕፃን ጸለይሁ፤ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል" (1 ሳሙኤል 1:27)

ሃና እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣት የጸለየችው ጸሎት ዘጠኝ ወራትን ብቻ ጠብቆ በቶሎ የተመለሰ ጸሎት ሊመስል ይችላል (1 ሳሙ 1:9-20)።





ነገር ግን ቀዳሚዎቹን ቁጥሮች ስናነብብ ይህ ጸሎት እንዲመለስ በጣም ረጅም ጊዜን መውሰዱን እናስተውላለን (1 ሳሙ 1:1-8)።

የሕልቃና ሁለተኛ ሚስት ፍናና "ብዙ ልጆች" ነበሯት ስለሚል ከአንድ በላይ ወንዶችን ወልዳ ነበረ። እግዚአብሔር የሃናን ማህጸን ዘግቶት ስለነበር ፍናና "ከዓመት ዓመት" ሃናን ታማርራት ነበር።

ከዚህ በመነሳት ሃና ልጅን እየጠየቀች መልሱ ሳይመጣላት የቆየው ለስንት ዓመታት ይሆን?





አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ዝምታ መንስኤው የእኛ ራስ ወዳድነት (ያዕ 4:3)፣ የምንወድደው ኃጥያት (መዝ 66:18)፣ እምነት ማጣት (ያዕ 1:6)፣ ወይም ለጥያቄያችን መልስ ትክክለኛው ጊዜ አለመድረስ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር አስቀድሞ መዳረሻችንን ያያል ለእኛም የሚበጀውን ከእኛ በላይ ያውቅልናል (ኤር 29:11)። በእምነት የቀረበውን ጸሎት በራሱ ጊዜ እና በራሱ መንገድ ሳይመልስ መቼም አይቀርም (1 ዮሐ 5:14-15)።

# አርአያ የሚሆኑ ጸሎቶች



# ኢየሱስ: የጸሎት ይዘት

"እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥" (ማቴዎስ 6:9)



በሰዎች ዘንድ አድናቆትንና ምስጋናን ለማግኘት በፊታቸው ረጅምና ዝርዝር ጸሎትን ማድረግ ኢየሱስ ያስተማረን የጸሎት መንገድ አይደለም (ማቴ 6:5-8)።





ጸሎታችን ልባዊና ቀላል ሆኖ በመደበኛ ቋንቋ ሊቀርብ ይገባዋል። ጸሎት የህይወታችን ዋና ክፍል ነው።

"በአጭሩና ትኩረቱን ባልሳተ መልኩ የሚያስፈልጋችሁን ብቻ በመጠየቅ መጸለይን ተማሩ። እግዚአብሔር ብቻ ሊሰማችሁ በሚችልበት ቦታዎች ላይ ደግሞ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ መጸለይንም ተማሩ። የግብዝነት ጸሎትን ትታችሁ ከልብ በሆነ መንፈስ የነፍሳችሁን የሕይወት እንጀራ ረሃብ ግለጹ።" (E.G.W. "Our high Calling", May 4)



# ኢየሱስ: የጸሎት ይዘት



ኢየሱስ የሰጠን የጸሎት አርአያ ይህ ነው:

| | |
|---|---|
| “በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ” | ከሰው ልጆች ሁሉ ፈጣሪ ጋር ያለንን የአባትና የልጅ ግንኙነት እውቅና መስጠት አለብን |
| “ስምህ ይቀደስ” | ለእግዚአብሔር ቅድስና እውቅና መስጠት በፊቱ በአክብሮትና በፍርሃት እንድንቀርብ ያደርገናል |
| “መንግሥትህ ትምጣ” | የኢየሱስን ምጽአት በጉጉት እንጠባበቅ |
| “ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን” | የመለኮትን ልዕልና እንቀበልና የእግዚአብሔር ፈቃ በህይወታችንና በዓለም ውስጥ እንዲፈጸም እንለምን |
| “የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን” | ለመኖር የሚያስፈልገንን አካላዊ ደግሞም መንፈሳዊውን ጨምረን እንጠይቅ |
| “እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን” | ንስሃ መግባት፣ ይቅርታን መለመንና እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንደሚለን ሁሉ እኛን የጎዱንን ሰዎች ይቅር ማለትም አለብን |
| “ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን” | በዚህ ዓለም ያለው ክፉ እንዳያገኘን ጥበቃንና ከለላን ከጌታ እንለምን |
| “መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን” | እኛ የሆንነው ፣ አለን የምንለውና የምንሰራው ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ እውቅናን እንስጥ። ክብርና ውዳሴ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው። |


# ዳንኤል: የጸሎት አወቃቀር

“ማቅ ለብሼ በአመድም ላይ ሆኜ ስጾም እጸልይና እለምን ዘንድ ፊቴን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀናሁ።”
(ዳንኤል 9:3)

በዳንኤል 9:4-19 ላይ የተዘገበው ጸሎት የጸሎትን አራት ዋና ክፍሎች ያቀርብልናል:



- ውዳሴ (ዳን 9:4)
- ንስሃንና ይቅርታ (ዳን 9:5-15)
- ልመና (ዳን 9:16-19)
- ምስጋና (ፊል 4:6)





ገብርኤል ወደ ዳንኤል የመጣው ዳንኤል ጸሎቱን በምስጋና ሳይጨርስ በፊት ነበር።

ይህ የጸሎት መዋቅር ለግል ብቻ ሳይሆን ለጉባኤ ጸሎትም ይጠቅመናል። “ንስሃንና ይቅርታን” የምንለምንበትን ክፍል እንደ ጸሎቱ አውድ ገጣሚ ማድረግ እንደሚገባን ግልጽ ነው።

ይህ መዋቅር የጸሎታችንን ትኩረት በእግዚአብሔር ላይ እንድናደርግ ይረዳናል፤ ጸሎታችን ከመለኮት መደብር እቃ የመግዣ “ዝርዝር” እንዳይሆንም ይከላከልልናል።



# ስለ ጸሎት አራት ጥያቄዎች

## እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ከሆነ መጸለይ ለምን አስፈለገን?

ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ከፍ ያደርገናል፤ ከእርሱም ጋር ያለንን ግንኙነት እንድንመረምርና በየዕለቱ ራሳችንን እንድንፈትሽ ይመራናል።

የምንለውን ባናውቅ እንኳን መንፈስ ቅዱስ ሊያግዘን ሁሌ ዝግጁ ነው (ሮሜ 8:26)።



## ሁሉም ደህና ከሆነ መጸለይ ለምን ያስፈልጋል?



ምንም ኃጢያት የሌለባቸው መላዕክት እግዚአብሔርን ያለመታከት ያመልኩታል። እኛስ ምን ያህል ልናመልከው ይገባናል?

ሁሉ ነገር መልካም ስለሆነልን እግዚአብሔር አያስፈልገንም ብሎ ማሰብ ትዕቢተኛነት ነው።

## ከማን ጋር እንጸልይ?

እንደአስፈላጊነቱ:

1. እግዚአብሔርን በግልና በቅርበት ልናወራው ስንፈልግ በድብቅ መጸለይ
2. በቤተሰብ ወይም በትንሽ ቡድኖች መጸለይ
3. በቤተክርስቲያን መጸለይ







## እግዚአብሔርን እንዴት እናድምጠው?



ይህን ለማድረግ የጠራውና ጤናማ የሆነው መንገድ ጸሎትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጋራ በማዋሃድ በግል ጊዜን መውሰዱ ነው። ይህን ስናደርግ አሳባችንን ባዶ ከማድረግና ውስጣችንን ብቻ ከመስማት መጠበቅ አለብን።

EGW (Our Father Cares, May 25)

“ጸሎታችን ጉድለታችንን በጥልቀት መረዳትና የምንሻቸውን ነገሮች ከልብ መፈለግ ከሌለበት ምላሽ አያገኝም። ነገር ግን መልሳችን ወዲያውኑ ባይመጣ ታክተን ልመናችንን ማቋረጥ የለብንም። “…መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል” (ማቴ 11:12)። በዚህ የተጠቀሰው ግፈኛነት ያዕቆብ እንዳሳየው አይነት ያለ ቅዱስ የሆነ አለመታከትን ነው። ራሳችንን ወደ ከረረ ስሜት ውስጥ መክተት ሳያስፈልገን በተረጋጋ መንፈስና በጽናት ከልመኖቻችንን ጋራ የጸጋውን ዙፋን ደጅ መጥናት አለብን። የእኛ ስራ ነፍሶቻችንን በእግዚአብሔር ፊት እያዋረድን፣ ኃጥያታችንን እየተናዘዝንና በእምነት እየበረታን ወደ እግዚአብሔር መጠጋት ነው።”